በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የአንግሊካን ቤተክርስቲያን

የቅዱስ ቁርባን :- ሥርዐተ አምልኮና የማለዳ ጸሎት

Amharic:

የቅዱስ ቁርባን እና የማለዳ ጸሎት በ2000 ዓ.ም ከሥርዐተ አምልኮ መጽሐፍ ላይ የተተረጐመ::

To use this translation please contact ACE in Addis Ababa + 251 11 6623578

ቅዱስ ቍርባን ፡ሥርዐተ አምልኮ

ቃላት በቀሚኑ ጋደል ብለው ሲጻፉ ተግባራትን የሚያስታውሱ ናቸው።
ቃላት በመደበኛው የሕትመት አጻጻፍ ሲጻፉ በአንድ ሰው የሚባሉ በጥቅሉም ቄሱ የሚናገራቸው ናቸው።
በቅንፍ ውስጥ ያሉ ቃላት እንደ አስፈላጊነቱ ልንጠቀምባቸው ወይም ላንጠቀምባቸው እንችላለን።
ቃላት በደማቁ የሕትመት አጻጻፍ ሲጻፉ (ከአርእስት በስተቀር) በጉባዔተኛው የሚባሉ ናቸው።

1. እንኳን ደህና መጣችሁ፡-
   የዕለቱን የአገልግሎት ርዕስ መግለጥና እንግዶችን እንኳን ደኅና መጣችሁ ማለት።

ሀ. መሰናዶ

2. *መዝሙር ይዘመራል*

3. ጌታችን በዚህ አለ
ሁሉም፡ መንፈሱም ከእኛ ጋር ነው።

4. ሁሉም፡ ሁሉን የምትችል አምላክ ሆይ፣
በፊትህ የተከደነ ምስጢር የሌለ፣
የሁሉንም ልብና ሐሳብ የምታውቅ፣
በሚያነሣሣው መንፈስህ ልባችንን አንጻ፤
በፍጹም እንድንወድህና በሚገባ ቅዱስ ስምህን
እንድናከብር፣
በክርስቶስ ጌታችን ስም
አሜን።

5. *ሁሉም* :- ጌታ ሆይ ማረን x 3
ክርስቶስ ሆይ ማረን x 3
ጌታ ሆይ ማረን x 3

6. **የንስሓ ጊዜ**

ለንስሓ የሚያዘጋጁ ቃላት ይነገራሉ

ሁሉም: **በምሕረት የተሞላህ አምላክ**
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት፣
በሐሳብ በቃልና በተግባር የበደልነውን በደል በፊትህ
እንናዘዛለን፤ በፍጹም ልባችን አልወደድንህምና
ባልንጀራችንንም እንደራሳችን አልወደድንምና
በምሕረትህ
ያላፈውን በደላችንን ይቅር በለን፤
ያሁኑን ማንነታችንን እንድናስተካክል ርዳን፤
ልንሆን የሚገባንን ምራን፤
ፍትሕን እናደርግ ዘንድ፣ምሕረትን እንወድ ዘንድና
ከአንተም ከአምላካችን ጋር በትሕትና እንሄድ ዘንድ
አሜን::

7. **ቄሱ የእግዚአብሔርን ምሕረት ያውጃሉ**
ሁሉን የሚችል አምላክ ምሕረትን ይስጣችሁ
ኀጢያታችሁንም ይቅር ይበል፤
ለዘላለም ሕይወትም ያብቃችሁ::
አሜን::

8. **የውዳሴ** *መዝሙር ይዘመራል*

ሁሉም :- **ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም፤**
ሰላምም በምድር ለሕዝቡ ሁሉ::

ጌታ አምላክ ሰማያዊው ንጉሥ ሆይ፣

ሁሉን የምትችል አምላክና አባት፣
እናመልክሃለን፣ እናመሰግንሃለን፤
ክቡር ነህና እንወድስሃለን።

የአብ አንድያ ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፣
የዓለምን ኀጢአት የምታስወግድ፣
የእግዚአብሔር በግ ጌታ አምላክ ሆይ፣
ምሕረትህን በላያችን አብዛ፤
በአብ ቀኝ ተቀምጠሃልና
ልመናችንን ተቀበል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣
አንተ ብቻህን ቅዱስ ነህና፤
አንተ ብቻህን ጌታ ነህና፤
አንተ ብቻህን ታላቅ ነህና፤
ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ፣
በእግዚአብሔር አብ ክብር፣
አሜን።

9. የዕለቱ የኀብረት ጸሎት

ሁሉም ለዕለቱ ጸሎት አሜን ይላሉ

ለ. የእግዚአብሔር ቃል የሚነበብት ጊዜ

10. የእግዚአብሔር ቃል ተነብቦ ሲያበቃ አንባቢው፡-
ይህ የጌታ ቃል ነው *ይላል።*
*ሁሉም ፡-*እግዚአብሔር ይመስገን *ይላሉ።*

11. *መዝሙር*

12. **የወንጌል ንባብ**
የወንጌል ንባብ ከተሰማ በኋላ አንባቢው:-

ሃሌ ሉያ ፣ሃሌ ሉያ፤
እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ይላል ጌታ፤
የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ
አይመላለስም፤ይላል::
ሃሌ ሉያ ፣ሃሌ ሉያ!

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ከ..... ይሰማል
ሁሉም :-አ ጌታ ሆይ ፣ክብር ላንተ ይሁን::

ወንጌል ተነቦ ካበቃ በኋላ
ይህ የጌታችን ወንጌል ነው::
ሁሉም :- አ ክርስቶስ ፣ምስጋና ላንተ ይሁን::

13. **የዕለቱ ስብከት**

14. **የኒቅያ የእምነት መግለጫ**

በእግዚአብሔር አብ ታምናላችሁን?

ሁሉም :- **አንድ አምላክ በሆነ ፣ሁሉን በሚችል ሰማይንና ምድርን፣ የሚታየውንና የማይታየውን ነገር ሁሉ በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን::**

በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ታምናላችሁን?

ሁሉም:- **ዓለም ሳይፈጠር የአብ አንድያ የባሕርይ ልጅ በሆነው፤**

ከአምላክ በተገኘ አምላክ፣ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፣
ከእውነተኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ አምላክ፣
በተወለደ እንጂ ባልተፈጠረ፣
ከአብ ጋር በባሕርዩ በተስተካከለ፣ሁሉ በእርሱ
በተፈጠረ፣እኛን የሰው ልጆችን ለማዳን ሲል ከሰማይ
በወረደ ፣በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም ሥጋን
በለበሰ፣ደግሞም ሰው በሆነ፣
በጴንጤናዊው ጲላጦስ እጅ ስለእኛ በተሰቀለ፣
መከራን በተቀበለ፣በሞተ፣በተቀበረ፣
በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈው በሦስተኛው ቀን
ከሙታን በተነሣው፣
ወደሰማያት ባረገው ፣በእግዚአብሔር አብ ቀኝ
በተቀመጠው ፣በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ተመልሶ
በክብር በሚመጣው፣ለመንግሥቱ ፍጻሜ በሌለው፣
በክርስቶስ ኢየሱስ እናምናለን።

በመንፈስ ቅዱስ ታምናላችሁን?

ሁሉም:- ጌታና ሕይወት ሰጪ በሆነው ፣ከአብና ከወልድ
በወጣው፣
ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት በሚመለክና
በሚሰገድለት፣
አስቀድሞ በነቢያቱ አፍ በተናገረው፣
በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን።
በአንዲት ሁለንተናዊትና ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን
እናምናለን።
በአንዲት ጥምቀት በኀጢአትም ስርየት እናምናለን።
የሙታንንም ትንሣኤና የሚመጣውንም ዓለም ሕይወት
ተስፋ እናደርጋለን።
አሜን።

15. **የምልጃ ጸሎት**

በምልጃ ጸሎት ብዙ ጊዜ ስለሚከተሉት አርእስት ይጸለያል፦

- ❖ ስለ ክርሰቶስ ቤተ ክርስቲያን ፣
- ❖ ስለ ፍጥረት ፣ስለ ሰው ልጆች ፣ስለ ባለ ሥልጣናት፣
- ❖ ባአካባቢያችን ስላለው ማኅበረ ሰብ፣
- ❖ በመከራ ውስጥ ስላሉ ሰዎች፣
- ❖ በሞት የተለዩንን ቅዱሳን በጸሎት ማስታወስ።

ከእያንዳንዱ የምልጃ ፀሎት በ ላ የሚሰጥ ምላሽ

ጌታ ሆይ፣ ስለ ምሕረትህ
ሁሉም **ጸሎታችንን ስማ።**

16. በመጨረሻም
ምሕረትን የተምላህ አባት ሆይ
ሁሉም፤ **ስለ ልጅህ ስለ መድኀኒታችን ስለ ኢየሱስ ክርሰቶስ ስትል ጸሎታችንን ተቀበል።**
አሜን።
17. በማለዳ የጸሎት ጊዜ የጌታን ጸሎት በሚከተለው መንገድ ማስተዋወቅ
አዳኛችን እንዳስተማረን በመተማመን እንጸልይ፦

ሁሉም :- **በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣**
ስምህ ይቀደስ ፤መንግሥትህ ትምጣ፤
ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች፣
እንዲሁ በምድር ትሁን።
የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን።
በደላችንን ይቅር በለን፤

እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል።
ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን፤
መንግሥት ያንተ ናትና፤ኃይልም ክብርም፣
ለዘለዓለሙ ::
አሜን።

በመጨረሻ ወደሚገኘው የመዝጊያ ክፍል (ሠ) እንሄዳለን

ሐ. የቅዱስ ቍርባን ሥርዓት

18. ሰላም

ቄሱ ስለ ሰላም የሚናገሩትን በሚከተለው ተሰማሚ አባባል ይደመድማሉ፦-

የጌታ ሰላም ዘወትር ከእናንተ ጋር ይሁን።
ሁሉም፦- ከእርስዎም ጋር ይሁን።

19. የቅዱስ ቍርባን መስናዶ

20. መዝሙር ሊዘመር ይችላል/መባ ይሰበሰባል/።
ጎብስቱና ወይኑ በጠረጴዛው /በመሰዊያው/ ላይ ይቀመጣሉ

21. መባው በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት ይቀርባል፦-

የተባረክህ የፍጥረት ሁሉ ጌታ አምላክ ሆይ፣ ከመልካምነትህ የተነሣ ይህንን ጎብስት ዐብረን እንካፈላለን፤ ምድር ያፈራችው ፣የሰው እጆችም የሠሩት ነው።ለእኛም የሕይወት እንጀራ ይሆንልናል።

ሁሉም :- እግዚአብሔር ለዘላለም የተባረከ ይሁን።

22. የተባረክህ የፍጥረት ሁሉ ጌታ አምላክ ሆይ፣
ከመልካምነትህ የተነሳ ይህንን ወይን ዐብረን እንካፈላለን፤
የወይን ፍሬ ፣የሰው እጆችም የሰሩት ነው :: ለእኛም የደህንነት
ጽዋ ይሆንልናል::

ሁሉም :- **እግዚአብሔር ለዘላለም የተባረከ ይሁን::**

23. **የምስጋና ፀሎት:** (*ጉባኤው እንደቆመ ይቆያል)*

ጌታ ከእናንተ ጋር ይሁን ::
ሁሉም:- **ከእርስዎም ጋር ይሁን::**

ልባችሁን አንሡ::

ሁሉም:- **ልባችንን ወደ ጌታ እናነሣለን::**

ለጌታ ለአምላካችን ምስጋና እናቅርብ::
ሁሉም:- **ምስጋናና ውዳሴ ልናቀርብ ይገባል::**

24. እውነተኛ ጌታ አምላክ ሆይ ፣
ከአፍህ በወጣው እስትንፋስ አማካኝነት፣
ቃልህን ተናግረህ ሁሉንም ነገር ወደ መኖር አምጥተሃልና
ምስጋናና ክብር ይገባሃል::
25. በአምሳልህ ቀርጸህ በሚያስደንቅ ገነት ውስጥ አኖርኸን::
ምንም እንኳን የዐመፅን መንገድ ብንመርጥ፣
አንተ ግን የራስህ የሆኑትን ልትተው አልፈቀድህም::

26. ወደ ጸጋህ ኪዳን መልሰህ መላልሰህ ሳብኸን::

ፍትሕን፣የምሕረትንና የሰላምን አገዛዝ እንጠባበቅ ዘንድ፣
ለሕዝብህ ሕግን ሰጠህ፤በነቢያትህም እኛን አስተማርህ።

27. የመንግሥትህን ምልክቶች በምድር ስንጠባበቅ ሳለን፣
በሰማያት ያሉትን የመላእክትን ዝማሬ እናስተጋባለን።
ዘወትርም እየወደስንህ እንዲህ ብለን እናዜማለን፦

28. ሁሉም፦ **ቅዱስ ፣ቅዱስ ፣ ቅዱስ ጌታ፣**
የብርታትና የኀይል አምላክ፣
ሰማይና ምድር በክብርህ ተሞልተዋል።
ሆሣዕና በአርያም ።
በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው።
ሆሣዕና በአርያም።

29. ጌታ አምላክ ሆይ፣
አንተ ብቻ በቅድስና የተሞላህ ነህ፤
ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን፣
በታላቅ ግርማና ሞገስ በዙፋንህ ተቀምጠሃል።
በልጅህ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ምድር መምጣት፣
በደካማው ስጋችን ፍፁም የሆነውን፣የፍቅርህን ብርታት
ገለጥህልን።

ሁሉም ፦ **አሜን ፤ጌታ ሆይ ፣እናምናለን።**

30. የሰውን ተፈጥሮ በመልበስ፣
ኢየሱስ የደኅንነትን መንገድ አሳየን፤
እስከ ፍጻሜውም ወደደን፤ ስለ እኛም ራሱን
ለሞት አሳልፎ ሰጠ፤ ለራሱ ስለሆነውም በመሞት፣
ከእርሱ ጋር በክብር እንነሳና እንነግስ ዘንድ፣
ከኀጢአት እስራት ነጻ አወጣን።

ሁሉም :- **አሜን ፤ጌታ ሆይ ፣እናምናለን::**

31. ለእኛ ሲል ራሱን አሳልፎ በሰጠባት በዚያች ሌሊት፣
እንጀራውን አንሥቶ አመሰገነ፤ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ
ሰጣቸው፤ እንዲህ ሲል:-
'እንካችሁ፣ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን
ለመታሰቢያዬ አድርጉት::'

ሁሉም :- **አሜን ፤ጌታ ሆይ፣ አናምናለን::**

32. እንዲሁም ከእራት በ ላ ጽዋውን አንሥቶ አመሰገነ፤
ሰጣቸውም፤እንዲህ ሲል:-
'ሁላችሁም ጠጡ፤ ይህ ጽዋ ስለ እናንተና ስለ ብዙዎች
የኀጢአት ይቅርታ የሚፈስሰው የዐዲስ ኪዳን ደሜነው፤
በጠጣችሁትም ጊዜ ሁሉ ይህን ለመተሰቢያዬ አድርጉት::'

ሁሉም :- **አሜን ፤ጌታ ሆይ ፣እናምናለን::**

33. ሰለዚህም በመስቀል ላይ የተቀበለውን መከራውንና ሞቱን
እናውጃለን፤ መቃብሩን ፈነቃቅሎ በመነሣቱ ደስ ይለናል፤
በሰማይ በቀኝህ በመቀመጡም ሐሤት እናደርጋለን፤
በክብር ተመልሶ መምጣቱንም እንናፍቃለን::

ሁሉም:- አሜን፤ጌታ ኢየሱስ ሆይ ፣ቶሎ ና ::

34. የተዋጀንበትን አንድና ፍጹም መሥዋዕት ስናስብ፣
አባት ሆይ ፣በመንፈስ ቅዱስህ እነዚህ የፍጥረትህ በረከቶች
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ይሁኑልን::

የክርስቶስን መልክ እንድንመስልና ራሳችንን ፍጹም መሥዋዕት አድርገን በፊትህ እንድናቀርብ እርዳን።

ሀሉም፡- **አሜን ፤መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ ና።**

35. ሕዝብህን በሞገስህ ዐስብ ፤
በምሕረትህም የልባችንን ጩኸት አድምጥ።
ምድርን ባርክ ፤ድውያንን ፈውስ ።
የታሰሩት ነጻ ይውጡ፤
ቤተ ክርስቲያንህንም በሰማያዊው ኀይል ሙላ።

ሀሉም ፦ **አሜን ፤መንፈስ ቅዱስ ሆይ ፣ና ።**

36. ዐዲስ ፍጥረታት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹማን ወደሚሆኑበት፣ (ከ...እና) ከቅዱሳን ሁሉ ጋር በመንግሥትህ ማዕድ ዙሪያ ወደሚታደሙበት፣ ሕዝብህን ከምድር ዳርቻ ሁሉ ሰብስብ።

37. በእርሱ ከእርሱ ለእርሱ ፣በመንፈስ ቅዱስ አንድነት ክብርና ግርማ ከዘላለም አስከ ዘላለም ሁሉን ቻይ አባት ለሆንኸው ለአንተ ይሁን።
ሁሉም ፡- አሜን ።

38. አዳኛችን እንዳስተማረን በመተማመን እንጸልይ፡-

ሁሉም ፡- **በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣**
ስምህ ይቀደስ ፤መንግሥትህ ትምጣ፤
ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች፣
እንዲሁ በምድር ትሁን።
የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን።
በደላችንን ይቅር በለን፤

እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል።
ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን፤
መንግሥት ያንተ ናትና፤ኃይልም ክብርም፣
ለዘለዓለሙ ።
አሜን።

39. ከክርስቶስ ሥጋ ለመካፈል ይህን እንጀራ እንቈርሳለን።

ሁሉም :- እኛም ብዙዎች ሆነን ሳለን አንድ አካል ነን፤
ሁላችን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና።

40. ስለእናንተ የተቈረሰውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን
ሥጋ ፤ስለናንተ የፈሰሰውን ደሙን በእምነት ቀርባችሁ ተቀበሉ።
ብሉ፤ጠጡም እርሱ ለእናንተ ሲል መሞቱን በማሰብ፣ በልባችሁም
ተመገቡት በእምነት ከምስጋና ጋር ።
41. *ሁሉም*:-
የዓለምን ኀጢአት የምታስወግድ የእግዚአብሔር በግ፣
ምሕረትህ በእኛ ላይ ይሁን።
የዓለምን ኀጢአት የምታስወግድ የእግዚአብሔር በግ ፣
ምሕረትህ በእኛ ላይ ይሁን።
የዓለምን ኀጢአት የምታስወግድ የእግዚአብሔር በግ ፣
ሰላምን ስጠን።
42. የዓለምን ኀጢአት የምታስወግድ የእግዚአብሔር በግ
ኢየሱስ፣ ወደ እራትህ የሚታደሙት ብፁዓን ናቸው።
ሁሉም:- ጌታ ሆይ አንተን ለመቀበል የተገባሁ አይደለሁም፤ ነገር
ግን ቃልህን ብቻ ተናገር፤ እኔም እፈወሳለሁ።

43. ቅዱስ ቊርባን ይታደላል።
ከሌላ አብያተ ክርስቲያናት የመጣችሁ ቅዱስ ቊርባን ለመውሰድ
የተገባችሁ ዐብራችሁን መካፈል ትችላላችሁ።
መካፈል ያልቻላችሁ ለቡራኬ ወደፊት መምጣት ትችላላችሁ።
ቅዱስ ቊርባን በሚታደልበት ጊዜ መዝሙር ሊዘመር ይችላል።

መ. የጉባኤው ፍጻሜ

44. ከቅዱስ ቊርባን በኋላ የዕለቱ የጎብረት ጸሎት ይቀርባል ::

45. *ሁሉም፦* የሁላችን አባት ሆይ፣
ምስጋናና ውዳሴ ላንተ እናቀርባለን፤
ከአንተ ርቀን ሳለን አንተ ግን በልጅህ አግኝተኸን ወደ ቤትህ መለስኸን::
በሞቱና በሕይወቱ ፍቅርህን ዐወጀ፤
ጸጋህን ሰጠን ፣የክብርንም በር ከፈተልን::
የክርስቶስን ሥጋ የምንካፈል እኛ ደግሞ፣
የትንሣኤውን ሕይወት አንኖራለን፤
ከእርሱም ጽዋ የጠጣን እኛ ለሌሎች ሕይወትን እናካፍላለን::
የበራልንን የመንፈሱን ብርሃን ለዓለም እንሰጣለን::
በፊታችን ላዘጋጀኸው ተስፋ ጽኑዓን አድርገን፤
እኛም የአንተ ልጆች ሁሉ ነጻ እንሆናለን፤
ምድርም ሁሉ ለስምህ ምስጋና ያመጣል፤
በክርስቶስ ስም::

አሜን::

46. መዝሙር ይዘመራል::

47. ቡራኬ፦ ጉባኤው እንደ ቆመ ይቈያል

አእምሮን ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም፣
በእግዚአብሔር እውቀትና ፍቅር፣በልጁም በኢየሱስ ክርስቶስ
ልባችሁንና ሐሳባችሁን ይጠብቅ።
ሁሉን የሚችል አምላክ በረከት፣
በአብ ፣በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ፣
ለዘወትር በመካከላችሁ ይሁን።
አሜን።

48. ጌታን ልትወዱና ልታገለግሉ በሰላም ሂዱ።

ሁሉም በክረስቶስ ስም ። አሜን።

49. አገልጋዮችና ምዕመናን ይሰናበታሉ።

ሠ. ለማለዳ ጸሎት በአማራጭነት የቀረበ
18. ሀ. ሰላም

19.ሀ. የመባ መዝሙር፡ - መባ ይሰበሰባል።

20.ሀ. መራ- በፍጹም ልባችሁ በእግዚአብሔር ታመኑ፤
በራሳችሁም ማስተዋል አትደገፉ።
ሁሉም ፡- በፍጹም ልባችን በጌታ እንታመናለን፤
በራሳችንም ማስተዋል አንደገፍም።
መሪ፡- በመንገዳችሁ ሁሉ ጌታን ዕወቁ፤
እርሱም ጕዳናችሁን ያቀናላችኋል።
ሁሉም ፡- በፍጹም ልባችን በጌታ እንታመናለን።
መሪ፡- ክብር ለአብ፣ ክብር ለወልድ ክብር ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን።
ሁሉም ፡- በፍጹም ልባችን በጌታ እንታመናለን፤
በራሳችንም ማስተዋል አንደገፍም።

21. መሪው እንዲህ ይላል፡-
አምላክ ሆይ፣ ልባችንን አቀጣጥል፤
ፍጻሜ የሌለው የፍቅርህ ነበልባል
በውስጣችን ነዶ ለሌሎች ብርሃን እንድንሰጥ።
በምድር ላይ እንዳለች ቤተ ክርስቲያንህ፣
ለዘለዓለም እያንጸባረቅን ለልጅህ ለመድኀኒታችን ለጌታ ለኢየሱስ
ክርስቶስ ክብር እንሰጣለን።
ሁሉም ፡- አሜን።

22. ሀ. መዝሙር ይዘመራል
23. ሁሉም ይህን ይላሉ ፡-
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር፣ የመንፈስ
ቅዱስም ኅብረት ከሁላችን ጋር ለዘለዓለም ይሁን።
አሜን።
24.ሀ. ጌታን እንድትወዱና እንድታገለግሉ በሰላም ሂዱ።
ሁሉም፡ በክርስቶስ ስም ።
አሜን።

Translated from Common Worship: Feb. 2009
By students of St Philip's School of Theology,
a part of the Anglican Church in Ethiopia (ACE),
under the guidance of Mrs. Mary Witts, Course Director.
The work was funded by USPG.
With grateful thanks to all those who did the translations, the checking, and proof-reading or who administered the process.